# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው - ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

39ኛ ዓመት ቁጥር 2 meison.hf@gmail.com ታህሳስ 2006


## ባለቤቱን ከአልናቁ..........

*በሳውዲ አረብያ በወገኖቻችን ላይ እየተፈፀመ ያለውን ግፍ በመቃወምና እንዲቆምም በመጠየቅ በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮድያውያን ከዚህ በፊት ባልታየ ቁጣና ህብረት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየደረጉ ይገኛሉ። እንዲህ አይነቱ ግፍ በሳውዲ አረብያም ሆነ በቀሩት አረብና የመሃከለኛው ምስራቅ አገሮች ሲፈፀም በርካታ አመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ አመታት ከሞላ ጎደል በየሳምንቱ ሊባል በሚችል ደረጃ "እዚህ አገር በደረሰባት እንግልት ተበሳጭታ አንዲት ወጣት ራስዋን ገደለች፣ እዚያ አገር አሰሪው ደብድቦ ገደላት፣ ሌላ ቦታ ደግሞ ባልፈፀመችው ግድያ ተወንጅላ የሚከራከርላት አጥታ በፍርደ ገምድል ውሳኔ በአደባባይ ተገደለች ወዘተ....." እየተባለ በተለይ የቤት ሰራተኛ በሆኑ እህቶቻችን ላይ የሚፈፀሙ ሰቆቃዊ ድርጊቶችን ስንከታተል ቆይተናል። የዛሬው ሁኔታ ከነዚህ የሚለየው ግፉ አይን በሚስብ መልክ ብቻ ሳይሆን በሽህና በደርን ሽህ በሚቆጠሩ ዜጎቻችን ላይ እየተፈፀመ በመሆኑና በዚህም የተነሳ ከዚሁ በሚመጥን ስፋት ኢትዮድያውያን "በቃ" ብለው በመላ አለም ከዳር ዳር መነሳታቸው ነው።*

*ቀውሱ ሰፊና ስር የሰደደ ቢሆንም በመፈፀም ላይ ያለው ግፍ ነገ ጋብ ያለ ቢመስል ችግሩ እንደተፈታ ተቆጥሮ ትግሉም ጋብ ሊል ይችላል የሚል ስጋት አለን። ይህ እንዳይሆን ከፈለግን የቀውሱን የተለያዩና ውስብስብ የሆኑ ገፅታዎች በሚገባ ተረድተን ለሁኔታው የሚመጥን የአጭርና ረዥም ጊዜ የትግል ስትራቴጂ መቀየስ ያስፈልጋል። ያለንበት ቀውስ ምንም እንኳን በጥብቅ የተያያዙ ቢሆኑም ሶስት ገፅታዎች አሉት።*

*የመጀመሪያው ገፅታ የችግሩን ስፋት ይመለከታል። በአለፉት አመታት ስራና ብሎም የተሻለ ኑሮ በመፈለግ ከሃገራችን በህጋዊ ብቻ ሳይሆን በህገ ወጥና ማፍያ ድርጅቶች አማካኝነት በሚልዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች ወደ አረብ አገሮች ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ወደ ተለያዩ አገሮች በተለይ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሲጎርፉ ታዝበናል። ሰሞኑን ይፋ የሆኑ አሃዞችን ብንመለከት ይህ ለስራ የመሰደድ አካሄድ ከአለፉት ሶስት አመታት ወዲህ እየተስፋፋ እንደሄደ እናያለን። አገር ቤት የሚታተመው አዲስ ፎርቱን*
*ጋዜጣ ኖቨምበር 3 ባወጣው እትሙ የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ጠቅሶ በአቀረበው አሃዝ መሰረት በነዚህ ሶስት አመታት ብቻ በተለይ ወደ አረብ አገሮች በህጋዊ መንገድ ለስራ የሄዱት ዜጎች ቁጥር 450 ሽ ሲሆን በህገ ወጥ ደላሎች አማካኝነት የሄዱት ደግሞ አንድ ሚልዮን ተኩል እንደሚደርስ ዘግቧል። እንዲህ አይነቱ ፍልሰት መከሰት ከጀመረ በርካታ አመታት የተቆጠሩ በመሆኑ በነዚህ አገሮች በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ የሚገኙ ዜጎቻችን ቁጥር ከዚህ እጅግ የሰፋ እንደሆነ መጠራጠር አይቻልም።*

*ሆኖም የችግሩ ስፋት የሚለካው በዚህ መልክ በፈለሱት ዜጎቻችን ቁጥር ብቻ አይደለም። እነዚህ ወገኖቻችን መጀመሪያውኑ ለስራ ወደ አረብ አገር የሚፈልሱት የራሳቸውን ኑሮ ለማደላደል ብቻ አይደለም። ደክመው በአፈሩት ገንዘብ በአገር ቤት በችግር ላይ ያሉ እናት፣ አባት፣ እህት ወንድም፣ ልጅ .....ያስተዳድሩበታል። በዚህ ቀውስ ሳቢያ ከዛው ከሳውዲ አረብያ አንድ ዜጋ በላከው መልእክት በዚች አገር ቁጥራቸው ግማሽ ሚልዮን የሚጠጋ*

ኢትዮጵያውያን ሲኖሩ በሃገራችን ለኑሯቸው በነሱ ላይ የሚተማመኑ ዜጎች ቁጥር ደግሞ ሁለት ሚልዮን እንደሚ ደርስ ጠቁሟል። ከበርካታ ተንታኞች እንደሚሰነዘረው ከሆነ አንድ ወይም አንዲት ለስራ የተሰደደ/የተሰደደች ወ ጣት በሃገር ቤት በአማካኝ ለአምስት ሰዎች መኖሪያ ይልካል/ትልካለች። በመሆኑም አሁን የተከሰተው ቀውስ በነዚ ህ አገሮች ባሉ ላይ ከሚፈፀመው ግፍ ዘልቆ በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ህልውናም የሚፈታተን ቀውስ ነው ማለት ነው።

በዚህ መልክ ዜጎች ዜጎች በተለይም ወጣቶች በሚልዮን እየተቆጠሩ ቢሰደዱ ለዚህ ሁሉ መነሾ የሆነው በሃገራችን ያለው አስከፊ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ቀውስ በዚህም የተነሳ ወጣቱ የሚዋዥቅበት የጅምላ ስራ አጥነት፣ የመናጢ ድህነትና የጨለምተኝነት አባዜ ነው። ለገጠመን ችግር ዘላቂ መፍትሄው ኢትዮጵያውያን በገዛ ሃገራቸው ሰርተው መኖር የሚችሉበት ሁኔታ ማመቻቸት ብቻ እንደሆነ ምንም አጠያያቂ አይደለም። ለዚህ እውንነት አስፈላጊ የሆነውን የስርአት ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል ፍሬ ለመስጠት ግዜ የሚጠይቅ ነው። ጥያቄው በገዛ ሃገራቸው መቆሚያ መቀመጫ አጥተው ፊታቸውን ወደ ባእድ አገር ለማዞር የተገደዱት ወጣቶችና ሃገር ውስጥ ያሉ ዘመዶቻቸው እስከዚያው ምን ይሁኑ የሚለው ጥያቄ ነው።

ይህ ደግሞ ወደ ቀውሱ ሁለተኛ ገፅታ ያመጣናል። ይኸውም እነዚህ ዜጎች ለስራ በሚሄዱባቸው ሃገሮች የሚገጥማቸውን ችግር የሚመለከት ነው። ከሃገር ፈልሶ ሌላ ሃገር ስራ መፈለግ ያለ ነገር ነው። በዚህ መልክ ስራ ፍለጋ የሚሰደዱ ዜጎችን መብት ለመጠበቅ በአለም አቀፍ ደረጃ በተለይም ደግሞ በአለም አቀፍ የስራ ድርጅት (አ ይኤልኦ) እየተረቀቁ የፀደቁና የሚከበሩ ስምምነቶች አሉ። እነዚህ ውሎች በርካታ ሲሆኑ ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በ ስራ ፍልሰት አገራቸውን ለቀው የሚሄዱ ዜጎች ሊደረግላቸው ስለሚገባው የመብት ጥበቃ አይኤልኦ ኮንቬንሽን 18 9 ተብሎ የሚታወቀው በተለይ የቤት ሰራተኞችን የሚመለከተው አለም አቀፋዊ ውል ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ ሰነ ድ መሰረት ለቤት ለሰራተኞች እንዲታወቁ ከሚጠየቁት መሰረታዊ መብቶች መሃከል በቀን የስራ ሰአት ከስምንት፣ በሳምንት ደግሞ ከአርባ ስምንት ሰአት እንዳይበልጥ፣ በአንድ የስራ ቀንም ቢሆን በመሃል የእረፍት ጊዜ እንዲሰጥ ፣ በሳምንት አንድ የእረፍት ቀን እንዲኖር፣ የወሊድ እረፍትና ማህበር የማቋቋም መብት እንዲታወቅላቸው ወዘተ የሚሉት ይገኙበታል።

ችግሩ እንደ ሳውዲ አረብያ አይነቶቹ አገሮች እነዚህን ውሎች የሚቀበሉም የሚያከብሩም አለመሆናቸው ብቻ አይደለም። ከዚህ አልፈው ተርፈው የራሳቸው የሆነ ግፈኛ ህግና አሰራር አላቸው። እርግጥ ይች አገር ከሞላ ጎደል እነዚህን መብቶች የሚያረጋግጥ እ.አ.አ በሴፕቴምበር 2005 ተሻሽሎ የፀደቀ የሰራተኛ አዋጅ አላት። ይህ የ ሰራተኛ አዋጅ ግን ለሁሉም የሚሰራ አይደለም። አንቀፅ 7 በዚህ አዋጅ የታወቁት መብቶች የቤት ሰራተኞችን አ ይመለከቱም ብሎ በግልፅ ይደነግጋል። ከዚህ ይልቅ እነዚህ የቤት ሰራተኞች የሚተዳደሩት በርካታ የሰብአዊ መብ ት ተሟጋች ድርጅቶች የዘመናዊ ባርነት አራማጅ በሚሉት "ካፋላ ስርአት" ወይም ስፖንሰርሽፕ ሲስተም ነው። በ ዚህ ስርአት መሰረት ሰራተኞች (በተለይም ደግሞ የቤት ሰራተኞች) ሙሉ በሙሉ በአሰሪው ቁጥጥር ስር ናቸው። ወደ ሳውዲ ለመግባትም ሆነ ወደ ሃገራቸው ለመመለስ እንዲሁም ሌላ ቦታ ለመቀጠር፣ የአሰሪው ፈቃድ ያስፈልጋ ቸዋል። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ ፓስፖርታቸውን እንደደረሱ ለአሰሪው የማስረከብ ግዴታ አለባቸው። ይህ አይነ ቱ አሰራር በአጠቃላይ በሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የተወገዘ ነው። አንዳንድ ዜጎቻቸውን በገፍ ወደነዚህ አገሮች የሚልኩ መንግስታት ደግሞ ከዚህ ዘልቀው ከመዳረሻ አገሮች መንግስታት ጋር እየተደራደሩ ሻል ባለ ሁኔ ታ የዜጎቻቸውን መብቶች ለማስከበር ይጥራሉ።

በዚህ የዜጎችን መብት በመንከባከብ ጉዳይ የፊሊፒንስ መንግስት ያደረገውን ብንመለከት ለአስፈላጊው በ ጎ ሂደት ጥሩ ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን። በሳውዲ አረብያ የባእድ ሰራተኞችን መብት የሚጥሰውን ስርአት በመቃወ ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2011 እ.ም. ጀምሮ የዚች አገር መንግስት ዜጎች ወደ ሳውዲ እንዳይሄዱ አግ ዶ ነበር። ከዚያ አያይዞ ግን በጉዳዩ ከሳውዲ መንግስት ጋር ሰፊ ድርድር አካሄደ። በአለፈው ሜይ ወር ሁለቱ መን ግስታት በዚህ ድርድር ሳቢያ የደረሱበትን የጋራ ስምምነት ይፋ አድርገዋል። በዚህ ሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት ከተደረሰባቸው ነጥቦች መሃከል ዋና ዋናዎቹ የቤት ሰራተኞች የወር ደመወዝ ከ1500 ሪያል ወይም 400 የአሜሪካን ብር እንዳያንስ፣ ለእነዚህ ሰራተኞች በሳምንት አንድ የእረፍት ቀን እንዲኖር፣ በቀን የእረፍት ሰአት እንዲወሰን፣ በ የአመቱ ከክፍያ ጋር እረፍት እንዲሰጣቸው፣ የሰራተኞቹን ፓስፖርትና የስራ ፈቃድ በአሰሪዎቹ ቅጥጥር የሚያደርገ ው አሰራር እንዲቆም፣ ሰራተኞች የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው፣ ከውጭው አለም በነፃ ግንኙነት የሚያደርጉበት ዘ

ዴ እንዲረጋገጥና በአጠቃላይ ሰብአዊ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው የሚሉ ናቸው። የዉሉን ተግባራዊነት በተጨባጭ ለመከታተል የሁለቱ መንግስታት ተወካዮች የተሰየሙበት የጋራ ኮሚቴ ተሰይሟል።

ይህ ደግሞ "የኛ" መንግስትና ስርአት በዚህ ቀውስ ውስጥ ያለው ሚና ምንድነው ወደሚለው የቀውሱ ሶስተኛና እንዲያውም ዋና ወደምንለው ገፅታ ያመጣናል።

መጀመሪያ ከፍ ብለን እንዳወሳነው ዜጎቻችን በገፍ ለመሰደድ የሚገደዱት በሃገራችን የተተከለው ግፈኛ ስርአት ይህ ነው ለማይባል ድህነት እየዳረገ ከስደት ሌላ ምንም አማራጭ ስለማይሰጣቸው ነው። የችግሩን ስፋትና አሳሳቢነት በሚገባ ለማጤን ከዚህ ከዛሬው ቀውስ ዘለቅ ብለን የአለንበትን ሁኔታ እንቃኝ። ጋለፕ (Gallup) የሚባለው የምርምር ተቋም በአለም ደረጃ ፍልሰትን በተመለከተ እአአ ከ2007 እስከ 2010 በመቶ አርባ ስምንት አገሮች ሶስት አመታት የፈጀ ጥናት አካሂዶ ነበር። በዚህ በመመርኮዝ Poential Net Migration Index (PNMI) በሚል ርእስ ይፋ ያደረገውንና በየድረገፆች በሰፊው የተተቸውን ጥናት እንመልከት። ጥናቱ ለመመለስ የሞከረው መሰረታዊ ጥያቄ በአለም ደረጃ ለአቅም የደረሰ ሰው ሁሉ ሃገሩን እየለቀቀ ወደ ፈለገው አገር የመሄድ መብት ቢታወቅለት በየትኞቹ አገሮች የኗሪዎች ቁጥር ይጨምራል በየትኞቹ ሃገሮች ደግሞ ይህ ቁጥር ይቀንሳል? የሚለው ጥያቄ ነበር። ውጤቱስ? እንደ አሜሪካና ካናዳ በአሉ ሃገሮች የህዝብ ቁጥር ከፍተኛ እድገት እንደሚያስመዘግብና በሲንጋፑር ለአቅም የደረሱ ኗሪዎች ቁጥር በ219% ኒፓውዚላንድ ደግሞ በ184% እንደሚጨምር ያሳያል። ከሁሉም ይበልጥ የህዝብ ፍልሰት ሊከሰትባቸው የሚችሉት ተብለው የሚጠቀሱት አምስት አገሮች ሁሉም ከአፍሪካ ሲሆኑ ኢትዮጵያ ናይጀሪያና ሱማሊያ ለአቅም ከደረሱ ዜጎቻቸው 46% ዚምባብዌ 47% ሴሪያሊዮን ደግሞ 56% እንደሚያጡ ይጠቁማል።

በሃገራችን የተተከለው ስርአት የችግራችን ዋና ምንጭ ሊባል የሚችለው በዚህ መልክ ዜጎችን ለፍልሰት የሚያመቻች ስርአት በመሆኑ ብቻ አይደለም። ሌላው ችግር ዛሬ በሳውዲና በሌሎች አረብ አገሮች ዜጎቻችን ላይ ከሚካሄደው ግፍ አንፃር እነሱን ለመታደግ ከፍ ብለን ከፊሊፒንስ ምሳሌ እንዳየነው ከአንድ መንግስት የሚጠበቀውን ተግባር አለማከናወኑ ነው።

በነዚህ አገሮች የሚገኙ ወገኖቻችን "ከኛ" መንግስት ይህ ነው የሚባል ድጋፍና እንክብካቤ አያገኙም። ባለፈው መጋቢት ወር በዚህ ጉዳይ የኢህአዴግ መንግስትና የአለም አቀፍ የስራ ድርጅት በአረብ አገሮች በሚገኙ የቤት ሰራተኞች ጉዳይና ወደነዚህ አገሮች በህጋዊ መንገድ ሲሄዱ ስለሚያስፈልጋቸው ስልጠናና ቅድመ ዝግጅት፣ በስራ ላይ እያሉ ስለሚደረግላቸው ጥበቃና እንክብካቤ፣ ወደ ሃገር ሲመለሱ ደግሞ ኑሯቸውን ለማደላደል ስለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ወዘተ... "የመግባቢያ ሰነድ" ወይም ሜሞራንደም ኦፍ አንደርስታኒዲንግ ተፈራርመዋል። ይህንን ለመተግበር ደግሞ የሚያስፈገውን ወጭ የአውሮፓ ህብረት የሚሸፍን መሆኑንና ከኢትዮጵያ በኩል የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ የአሰሪዎች ማህበርና የሰራኞች ኮንፌዴሬሽን ተወካዮች ያሉበት ከአይኤልኦ ጋር የሚሰራ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ለቤት ስራ ወደነዚህ አገሮች ለሚፈልሱ ዜጎች የእንዲህ አይነቱ አካሄድ አስፈላጊነት የሚያጠራጥር አይደለም። ችግሩ አንደኛ ይህ ስምምነት የሚያወራው በህጋዊ ዘዴ ስለሚፈልሱ ዜጎች ብቻ ነው። ከፍ ብለን እንዳየነው ወደነዚህ አገር የሚጎርፉት ሰራተኞች በአመዛኙ በህገ ወጥ ዘዴ የሚፈልሱ ቢሆኑም ይህ ሰነድ እነሱን አይመለከትም። ሁለተኛና ዋናው ችግር ሳውዲ አረብያ ለዚህ ላልፈረመችው ውል እንድትገዛ የሚያስገድዳት ምንም ምክንያት አለመኖሩ ነው።

በመሆኑም ከዚህ ይልቅ ትክክለኛና ውጤታማ ይሆን የነበረው አካሄድ ልክ እንደ ፊሊፒን መንግስት የኛዎቹም ከዜጎቻችን መዳረሻ አገሮች ጋር በቀጥታ መደራደርና በነዚህ አገሮች በአሉ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎቻችን አማካኝነት በተጨባጭ የዜጎቻችን መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበር። ይህ ግን አልሆነም። ከዚህ ይልቅ እየተሞከረ ያለው አሁን እንደምናየው ዜጎች ለስራ ወደ ሳውዲ እንዳይሄዱ የማገድ አካሄድ ነው። ይህ ጨርሶ አይሰራም። አንደኛ አካሄዱ በህጋዊ መንገድ ቪዛ እየተሰጣቸው የሚሄዱትን ዜጎች ብቻ በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ከሃገር የሚወጡትን የማይመለከትና ውሎ አድሮ ደግሞ ይኸኛውን አደገኛ የሆነ አካሄድ የሚያበረታታ እንጂ ፍልሰቱን የሚገታ አይደለም። ሁለተኛ ደግሞ በህጋዊ ዘዴ ወደ ሳውዲ ለመሄድ የሚፈልጉ ዜጎች ይህንን እገዳ ለመወጣት መጀመሪያ በካርቱም የማለፍ አካሄድ በመያዛቸው ሰሞኑን አዲስ አበባ ያለው የሱዳን ኤምባሲ በቪዛ ጠያቂዎች ሲጨናነቅ ይታያል። እንዲህ አይነቱ ፍሬ ቢስ ሙከራ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ሌላውን መሰረታዊ ጥያቄ ማለትም ከ

ወዲሁ በሳውዲ መንግስት ጋር ተደራድሮ በዚች አገር የሚገኙት ዜጎቻችንን መብት የማስከበሩን ጉዳይ የሚመለስ አይደለም።

ለዚህ አስፈላጊ የሚሆነውን ድርድር ለማካሄድ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ፍላጎቱም ብቃቱም የለውም። ሳውዲዎች በገዛ ሃገራቸው በዜጎቻችን ላይ የሚፈፅሙትን ግፍ መከላከል ቀርቶ ከቅርብ ጊዜ ጠዲህ እየተሳፋፋ በ መጣው "ሁለተኛው መራኮት ለአፍሪካ" በተሰኘው አዲሱ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሳቢያ በሃገራችንም ለሚፈፅሙ ት ግፍ አባሪ ተባባሪ የሆነ መንግስት ነው። በእዚህ "ላንድ ግራብ" በተባለው ባእዳን ባለሃብቶች በመሬት አጋባሽነት ፣ የአፍሪካ አገሮች ሙሰኛ ልሁቃን ደግሞ በመሬት ቸብቻቢነት በተሰለፉበት ሂደት ድሃ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎ ች ይህ ነው የማይባል የኑሮ መመሰቃቀል እየገጠማቸው ነው። ሁማን ራይትስ ወችን ጨምሮ በርካታ የሰብአዊ መ ብት ተሟጋች ድርጅቶች ከሚያቀርቡት አሃዞች እንደሚታየው በኛ አገር በተለይ ከጋምቤላ፣ አፋርና ቤኒሻንጉል አ ንድ ሚልየን ተኩል የሚሆኑ ዜጎች ከመሬታቸው ከኑሯቸው ተፈናቅለዋል። በዚህ ቻይናዎች፣ ህንዶች፣ የጎልፍ አ ገሮች በሚሳተፉበት የመሬት ማጋበስ ሂደት ሳውዲ አረብያም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆና ትታያለች። የሙሰኞቹ የ ኢህአዴግ መሪዎች ጭንቀት የወገኖቻችን ሰቆቃ አይደለም። ከዚህ ይልቅ አካሄዳቸው ይህ መሬት አጋባሾቹና ቸር ቻቢዎቹ በሃገራችን ድሃ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች ኪሳራ የተሳሰሩበት የጥቅም ግንኙነት እንዳይሻክር ላይ ታች ማለት ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ስጋታቸው ደግሞ ያለምክንያት አይደለም።

አሁን በተከሰተው ቀውስ ሳቢያ በሃገራችን ባሉት የሳውዲ ኢንቬስተሮች አካባቢ ጭንቀት እየተፈጠረ በ መሆኑ አንዳንዶቹ ሃገር ለቀው ለመውጣት እያሰቡ ናቸው። ከስልሳ በላይ የሚሆኑ ባለሃብቶች አባል የሆኑበት "በኢ ትዮጵያ የሳውዲ እርሻ ኢንቬስተሮች ማህበር" በሚባል የሚታወቀው ስብስብ ፕሬዜዳንት የሆኑት መሃመድ አል ሻህሪ ዲሴምበር 9 Al Monitor News Letter ለተባለው የመካከለኛው ምስራቅ ጋዜጣ በሰጡት ማብራሪያ ይህንኑ ስጋት ገልፀው የመፍትሄም ሃሳብ ያቀርባሉ። ሰውየው የተፈጠረው ቀውስ በተለይ በተቃ ዋሚ ጋዜጦች አራጋቢነት በህዝቡ ፀረ ሳውዲ ስሜት እየፈጠረ አንዳንድ ባለሃብቶችን ሃገር ለቀው እንዲወጡ አይ ገፋፋቸው መሆኑን ይገልፃሉ። ከዚህም ተነስተው የኢትዮጵያ መንግስት አስፈላጊውን ጥበቃ ለማድረግ ያለውን ቅ ርጠኝነት በማውሳት
በነዚህ ባለሃብቶች አካባቢ እየተፈጠረ ያለውን ስጋት ለመቅረፍ ይሞክራሉ። ከዚያም አከታትለው የቀውሱ መንዛዛ ት በነዚህ ኢንቬስተሮች አካባቢ ያለውን የአለመረጋጋት ስሜት እንዳያባብሰው ሁለቱ መንግስታት ተደራድረው በአ ስቸኳይ ለችግሩ መፍትሄ እንዲሹ ይማጠናሉ።
የኢህአዴግ መንግስት የተያያዘው አካሄድ በሳውዲዎቹ ኢንቬስተሮች ዙሪያ የተከሰተውን ይህንን የአለመረጋጋት ስ ሜት ለማርገብ ከሁለት አንፃር የሚጥር ሆኖ እናገኘዋለን።

የመጀመሪያው መሃመድ አልሻህሪ "በተቃዋሚዎች አራጋቢነት" እየተስፋፋ ነው የሚሉትን ፀረ ሳውዲ ስ ሜት ለማፈን የሚደረግ ሙከራ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ አይን ባወጣ መልኩ የታየው በሃገራችን የህዝብ ተቃውሞ ይፋ እንዳይወጣ የተወሰደው እርምጃ ነው። የሳውዲዎቹን ግፍ በመቃወም በመላው አለም የተቃውሞ ሰልፎች ሲካ ሄዱ የኢህአዴግ መሪዎች ዜጎች በዚያው በሃገራችን ይህንን ተቃውሞ እንዳያሰሙ ሰልፍ ሲከለክሉና መሪዎችን ሲ ያስሩና ስያንገላቱ አይተናል። የሰዎቹ አስተሳሰብ ጨርሶ የተገላቢጦሽ በመሆኑ ይህንን ሰልፍ ሲከለክሉ የሰጡት አ ስገራሚ ምክንያት ወይም ሰበብ በሁለቱ አገሮች መሃከል ያለውን መልካም ግንኙነት ላለማሻከር የሚል ሆኖ እናገኘ ዋለን። ማለትም የተባለው ግንኙነት የሚሻክረው ሳውዲዎቹ በዜጎቻችን ላይ በሚፈፅሙት ግፍ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ግፍ ተቃውሞ መንቀሳቀሱ ሆኖ ቀርቧል።

የኢህአዴግ መንግስት አካሄድ በዚህ መልክ የህዝቡን ተቃውሞ ለማፈን በሚወሰዱ እርምጃዎች የሚወሰን አይደለም። ከዚህ በተያያዘ በቀውሱ ሳቢያ ሳውዲዎች በሃገራችን ያላቸው የኢኮኖሚ ጥቅም በምንም አይነት ጥያ ቄ ውስጥ እንደማይገባ ዋስትና የመስጠት ባለሃብቶቹን የማረጋጋት ሙከራ እየታዘብን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይ ለማርያርም ደሳለኝ ህዳር 21 ቀን ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሰጡት ማብራሪያ በሁለቱ ሃገሮች መሃከል የቆየ ግንኙነ ት መኖሩን ከገለፁ በኋላ "በዚች አሁን በተከሰተችው ቀውስ" (የሳቸው አባባል ነው) ምክንያት ይህ ግንኙነት እንደ ማይለወጥና ለወደፊቱም ተጠናክሮ እንሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልፀዋል። በአሁኑ ወቅት የአለምን ቀልብ የሳበ ውና ቁጣ የቀሰቀሰው በሳውዲ በዜጎቻችን ላይ በመፈፀም ላይ ያለው ግፍ ሲሆን በሪያድ ያሉት የኢትዮጵያ አምባ ሳደርም የሳውዲዎቹ ጥቅም በዚህ ቀውስ ምክንያት የማይነካ መሆኑን ለማስረገጥ ሲሞክሩ እናያቸዋለን። 7 ዲሴም

በር በአረብ ኒውስ በታተመ መግለጫ በሳውዲና በኢትዮድያ መካከል ያለው የኢኮኖሚ ግንኙነት ምን ያህል ስር የ
ሰደደ መሆኑን ለማመልከት መንግስታቸው ለ361 የሳውዲ ኢንቬስትሜንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ የሰጠ መሆኑንና ከነ
ዚህ ውስጥ ከወዲሁ 125 በተግባር ላይ እንደዋሉ ገልፀዋል። ከቀውሱ ባሻገር መቀጠል ያለበት ይህ ግንኙነት ለሳው
ዲዎች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮድያውያንም ጠቃሚ መሆኑን ለማስረገጥም በስራ ላይ በዋሉት ፕሮጀክቶች አማካኝነት
ለ35ሽ ዜጎች የስራ እድል መከፈቱን አብስረው የመጣ ቢመጣ ይህ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በቀው
ሱ ምክንያት ጥያቄ ውስጥ አይገባም በፖል መንፈስ ሳውዲዎቹን ለማረጋጋት ሞከረዋል።

ይህን ሁሉ ስናይ ከሳውዲዎቹ አካሄድ በስተጀርባ ያለውን ስሌት መገመት አስቸጋሪ አይደለም። በገዛ ሃገራ
ቸው ቀርቶ በኛም በራሳችን አገር በዜጎቻችን ላይ ይህንን ሁሉ ግፍ ሲፈፅሙ በጥቅም የተንበረከኩላቸው ገዥዎቻ
ችን "በቃችሁ" እንደማይሏቸው ጠንቅቀው ያውቃሉና አካሄዳቸው "ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ" በሚለ
ው አባባል የሚመራ እንደሆነ ግልፅ ነው። በሳውዲ አረብያ ስለ ኢትዮድያ መንግስት አልባነት የሚንፀባረቀው አስ
ተሳሰብ በመንግስት ደረጃ የሚወሰን አይደለም። ኖቨምበር 24 በታተመው ሪፖርተር ጋዜጣ አንዲት ወጣት ከሪያድ
ስልክ ደውላ የድረሱልን ጥሪ ስታስተላልፍ ፖሊሱም፣ ጋጠወጦቹም ሲደበድቧቸው "እናንተ የተጣላችሁ፣ መንግስ
ት የላችሁም፣ አንፈልግም ብለናችኋል!" እንደሚሏቸው ገልፃለች። ይህንን እውነታ እኛም ብንሆን እናውቀዋለን።
ከዚህ ተነስተን ሃገራችን በመንግስት ደረጃ ባይሆንም ሊንቁት የማይችሉት ለመብቱና ለክብሩ የሚቆም ህዝብ ያለባ
ት አገር መሆኗን ለማስረገጥ የተያዘው የተቃውሞ እንቅስቃሴ መቀጠሉ ወሳኝ ነው። ይህንን ስናደርግ ግን ከአእም
ሯችን መጥፋት የሌለበት አንድ ቁም ነገር አለ። በመፈፀም ላይ ካለው ግፍ ባሻገር በሳውዲ በአስቸጋሪ ሁኔታም ስ
ር ቢሆኑ ሰርተው የራሳቸውንም ሆነ አገር ቤት ያሉ ዘመዶቻቸውን ህልውና መልክ ለማስያዝ የሚጥሩ በመቶ ሽህ
የሚቆጠሩ ዜጎቻችን አሉ። በመሆኑም ተቃውሟችን ከወዲሁ አስቸጋሪ የሆነውን የእነዚህ ወገኖቻችንን የሳውዲ ቆ
ይታ የባሰ ችግር ላይ እንዳይጥል፣ በተለይም ደግሞ ከጋጠ ወጦች የሚሰነዘርባቸውን የወከባ ውርጅብኝ ሳለማገዝ
ከጥላቻ አንፀባራቂ መፈክሮች፣ ከአጉል ድንፋታዎችና ከዘረኛ ፀረ አረብ መፈክሮች የፀዳ በኢትዮድያዊ ጨዋነት
መንፈስ የሚካሄድ ተቃውሞ መሆን ይኖርበታል።

ግን ይህ ብቻውን በቂ አይደለም። ከዚህም በማያያዝ ከአለንበት ዙሪያ ገጠም ቀውስ ለመውጣት ዜጎችን
በገዛ አገራቸው ሰርተው እንዳይኖሩና ፊታቸውን ወደ ባእድ አገር እንዲያዞሩ የሚገፋፉቸውን ሙሰኛና ፀረ ዴሞክራ
ሲያዊ ስርአት አስወግዶ ተጠያቂነት በተረጋገጠበት ስርአት ለመተካ ትግላችንን ማፋፋም ይኖርብናል። ለዚህ ብሄራ
ዊ አጀንዳ እውንነት ሲባል ደግሞ በተከሰተው ቀውስ ሳቢያ ኢትዮድያውያን ባሳዩት የትብብር መንፈስ ቀጥለው ት
ግላቸው ከሳውዲዎች ይልቅ በዚህ አጥፊ ስርአት ላይ ያነጣጠረ መሆን ይኖርበታል። በዚህ ቀውስ ልቡ የቆሰለውና
ለትግል የተነሳሳው ዜጋ ሁሉ ከስርአት ለውጥ በመለስ ለሃገራችን ምንም መድህን እንደሌለና ለዚህ ደግሞ ከጋራ
ተጋድሎ ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለ በመገንዘብ አሁን በተያዘው መልክ በአንድነት ለመንቀሳቀስ ሁሉም የተቻ
ለውን መስራት ይጠበቅበታል።

መላ ኢትዮድያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
ታህሳስ 2006 አ.ም.